# ETHIOPIAN
## CIVIL SERVICE UNIVERSITY

QUARTERLY MAGAZINE
Sept-Dec. 2022



**BUILDING CAPACITIES IN THE PUBLIC SERVICE THROUGH SPECIALIZED EDUCATION, TRAINING, CONSULTANCY, RESEARCH AND COMMUNITY SERVICES**

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

## ራዕይ

ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን

## ተልዕኮ

ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን
በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣
በስልጠና፣ በማማከር፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች
በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ልቆ መገኘት
ተባብሮ መሥራት
ሁሌም መማር
ፈጠራን ማበረታታት
ዘለቄታዊ ውጤታማነት
ብዝሀነትን መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

## Table of Contents

*ECSU Registrar and Alumni Directorate Gives Orientation* 1

‘በሀገረ-መንግስት ግንባታ የምሁራን ሚና” በሚል መሪ ሀሳብ የውይይት መድረክ ተካሄደ 2

ኢሲሰዩ የዓለም አቀፍ የፀረ- ሙስና ቀን አከበረ 4

የስልጠናና ማማከር ዘርፍ በሴክተር-ተኮርና የብቃት-ተኮር የስልጠናና የማማከር አገልግሎት አሰጣጥ ዙርያ አውደ-ጥናት አካሄደ 6

ኢሲሰዩ የ2015 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ግምገማ አደረገ 8

**Editor In -Chife**
**Tariku Ayano**
**Editors**
**Anteneh Demissie**
**Meley Tekeste**
**Photograph**
**Ibsa Bekele**

## *ECSU Registrar and Alumni Directorate Gives Orientation*

Ethiopian Civil Service University Registrar and Alumni Directorate gave orientation for new students who joined the university in the 2022/23 academic year on November 09/11/2022 at Abay Hall.



On the program, Dr. Lemma Gudissa, ECSU Academic Vice President, welcomed the students and gave a brief explanation about the overall activities and achievements of the university in building the capacity of the public sector. He also wished a successful learning time to all students and advised them to properly utilize the opportunity they got by joining the university.

ECSU Registrar and Alumni Directorate Director Dr. Abdu Mohammed on his part also welcomed the students on the behalf of the university community and explained to them the rules and regulations that they need to strictly follow



during their stay at the university. College deans and different directorate directors that have direct contact with students on their part also welcomed the students and wished successful learning time and explained the rules and regulations of their respective offices for smooth communication in their daily activities.



## “በሀገረ-መንግስት ግንባታ የምሁራን ሚና” በሚል

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ “በሀገረ-መንግስት ግንባታ የምሁራን ሚና” በሚል መሪ ሀሳብ ከታህሳስ 24 እስከ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የቆየ ለ4 ቀናት በሁለት ዙር ከዩኒቨርስቲዉ የአካዳሚክ ሰራተኞች ፣የአስተዳደርዘርፍ ዳይሬክተሮች እና ከቡድን መሪዎች ጋር ሲካሄድ የነበረዉ ዉይይት ተጠናቋል፡፡

በውይይቱ መክፈቻ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ ስለውይይቱ አስፈላጊነት ሲያብራሩ አሁን ባለው የዓለማችን ነባራዊ ሁኔታ ከምንግዜውምበላቀሁኔታሀገራትበጥንቃቄየሚመሩበትመሆኑን አመልክተው ሀገራችን ኢትዮጵያም ካለችበት የጂኦፖለቲካል ሁኔታ ካላት የዳበረ ታሪክና የሰው ሀብት እንዲሁም በዓለማችን



ላይ ያሉ ትላልቅ ሀገራት በዙሪያችን የጦር ሰፈር የመገንባት እንቅስቃሴና የራሷን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በምታደርገው ጥረት እየደረሰባት ባለው ተፅዕኖ ምክንያት ምሁራን ሊወጡት የሚገባው ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑን አመላከተዋል፡፡ በዚህም ረጅም የሀገረ መንግስት ግንባታ ታሪክ ያለው ሀገር በአንዳንድ ክስተቶች ሀገር ችግር ውስጥ የሚገባበት ምክንያት ምንድን እንደሆነ፣ በትምህርት ስርዓታችን ውስጥም ምን እንደጎደለ እንዲሁም ውስጣዊ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ምሁራን የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የሚያደረግ ውይይት መሆኑን በማስገንዘብ ተሳታፊዎች በውይይቱ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ አሳስበዋል፡፡

ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በበኩላቸው ለውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች እንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ በማስከተልም ምሁራን ለሀገር ስልጣኔና ዕድገት ጉልህ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን በማብራራት የሀገራችን መፃኢ ዕድል በእጃችን ላይ እንዳለ በመገንዘብ ታሪካዊና ሞራላዊ ግዴታችንንመወጣትይገባናልብለዋል፡፡“ምሁርለሌላዉትሩፋት መሆን አለበት” ሀገር የሚገነባዉ በተቋም ነዉ፤ ተቋም በሌለበት ሀገር የለም ለዚህ ደግሞ ምሁራን ሀላፊነት አለብን ብለዋል ፡፡

በመቀጠልም በሁለት ዙር በዶ/ር ለማ ጉዲሳ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት «በሀገረ መንግስት ግንባታ የምሁራን ሚና» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሀገራዊ ሰነድ ቀርቦ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በስፋት ተወያይተውበታል፡፡ የውይይት መድረኩን በዚህ ወቅት ለማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሀገር ያለንን አቅም ሁሉ አስተባብረን በጋራ ቆምን ሀገራችንን ለማበልፀግ፣ በምሁራን አማካይነትም መጪውን ውስብስብና የውድድር ዓለም እንዴት አሸናፊ ሆኖ መውጣት እንደሚቻል መፍትሔ ማማልከት እና እንደ ሀገር ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተገኙ ስኬቶች የነበሩና የቀጠሉ ርብርብ የሚሹ ጉዳዮች ላይ በጥልቀት መወያየት አስፈላጊ መሆናቸው በዶ/ር ለማ ጉዲሳ በቀረበው ዶክመንት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዶክመንቱም በሀገሪቱ የተከናወኑ የሪፎርም ስራዎች ያጋጠሙ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮችና ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች የቀረቡ ሲሆን በቀጣይ ሥራዎች ላይ የምሁራን ሚና በዋናነት ሊያተኩርባቸው የሚገቡ እንደ የፖለቲካ ገበያን መገንዘብና በሀገር ላይ የተደቀነውን ፈተና መታገል፣ የፖለቲካ

ገቢያ ተፅዕኖ እና የኒዮፓትሪሞኒያሊዝም ጋብቻ ፣ የአክራሪነትና የፖለቲካ ገበያ ትስስር፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ገበያ አዝማሚያ፣ ዘላቂ አወንታዊ ሰላምና ስልጡንና ዲሞክራቲክ ማህበረሰብ መገንባት እና ሌሎችም ሀሳቦች በስፋት ተነስተዋል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በብርቱ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈችን ሀገር ረጅም ዘመን የመንግስት ታሪክ ባለቤት በሆነች ሀገር ውስጥ የሀገር መንግስት ግንባታ ያልተጠናቀቀው ምን ቢጎድለን ነው፡፡ ላሊበላ፣ አክሱም፣ ጎንደርን ወዘተ የሰሩ ሰዎች የነበሩባት ሀገር እንዴት ለዘመናት የሚሻገሩ ህንፃዎችንና መንገዶችን የሚሰሩ መሀንዲሶችን ማፍራት ተሳናት ? በጋራ ሞተው ሀገር የሚታደጉ ዜጎች ባሉበት ሀገር እንዴት በጋራ ቆመን ከድህነት መውጣት ተሳነን ? ኢትዮጵያ ባሏት እሴቶች የሚኮራ ትውልድ እንዴት ሁል ጊዜ የመጤ ሀሳብና ርዕዮተ-ዓለም እየተጨቃጨቀና እየተከራከረ ሀገር ለማፍራት ይታትራል? እንዲሁም ለኢትዮጵያ መለወጥ ዋጋ ከፍሎ ዕድል ፈጥሮ ሲያበቃ የተገኘውን ዕድል ገፍቶ ወደ ተሟላ ድል መቀየር እንዴት ለተደጋጋሚ ጊዜ ይከብዳል? በሚሉ ዓበይት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ውይይት የተደረገ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ምሁራንም ከላይ በተነሱ ርዕሰ-ጉዳዮችና በሌሎችም ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይትና ጥያቄዎች ያቀረቡ ሲሆን በተነሱት ሀሳቦችና ጥያቄዎችም በዉይይተቶቹ መድረክ ማጠቃለያ ላይ ክቡር ዶ/ር ቀነአ ያደታ የመንግስት ተወካይና ዶ/ር



ዶ/ር ለማ ጉዲሳ አካዳሚክ ም/ፕሬዚደንት

ተመስገን ቡርቃ የኢ.ሲ.ሰ.ዩ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡በመጨረሻም አወያዮቹ ክቡር ዶ/ር ቀነአ ያደታ እና ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ እንዳሉት መንግስት ወደፊት ተከታታይ የዉይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ችግሮችን በዉይይት ለመፍታት ቁርጠኛ መሆኑን በመግለጽ እንዲህ አይነት መድረክ በቀጣይነት ስርአት ተበጅቶለት ተቋማዊ በማድረግ በቋሚነት እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡ ዉይይቱም በስኬት በመጠናቀቁ ለተሳታፊዎቹ ምስጋና አቅርበዋል፡፡







# ኢሲሰዩ የዓለም አቀፍ የፀረ- ሙስና ቀን አከበረ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ 18ኛ ጊዜ የሚከበረዉን የፀረ- ሙስና ቀን «ሙስናን መታገል በተግባር» በሚል መሪ ቃል ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲዉ ህዳሴ አዳራሽ በተለያዩ ዝግጅቶች አከበሩ፡፡




ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት



ዶ/ር አለማየሁ ደበበ የም/ ማ/ አ ም/ፕሬዚዳንት

በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ እንዳሉት ይህን ቀን ስናከበር በዋናነት ቀኑን ማስታወስ ብቻ ሳይሆን ሙስና የሚያስከትለዉን ጉዳት በመገንዘብ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን መጠየፍ በተጨማሪም በተግባር መታገል ያስፈልጋል፤ ለዚህም በተቋማችን ለምናደርገዉ የጸረ ሙስና ትግሎች በንቃት በመሳተፍ እያንዳንዳችን ጉልህ ድርሻ መወጣት አለብን ብለዋል፡፡ አመራሩ በምንም አይነት ሁኔታ ሙስናን እያየ የሚያልፍበትአካሄድእንደሌለበመግልጽበቅርቡምበተቋሙ ያለአግባብ ያልተገባ ጥቅም ሲወስዱ የተገኙ ሰራተኞች ከስራ ማሰናበቱን ገልጸዋል፡፡ይህ ተግባር ወደፊት የሚቀጥል ሲሆን አመራሩ እና ሰራተኛዉ ብልሹ አሰራር እንዳይታገስ በጸረ ሙስና ትግሉም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንአበክረዉ አሳስበዋል፡፡



በእለቱም በዶ/ር አለማየሁ ደበበ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ሙስናን መታገል በተግባር በሚል ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን በጽሁፉም ላይ ጠለቅ ያለ ዉይይት ተካሂዷል፡፡ በማስከተልም «የሙስና ተጋላጭነት



ዶ/ር ብርሀኑ በላይነህ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት» በሚል ርእስ ጥናታዊ ጽሁፍ በዶ/ር ብርሀኑ በላይነህ የቀረበ ሲሆን ተሳታፊዉች በቀረበዉ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ ዉይይት አድርገዋል፡፡

በመጨረሻም ከተሳታፊዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዚዳንት ሰፋ ያለ ማብራርያና ምላሽ የሰጡ ሲሆን በአጠቃላይ ሙስና ከመታገል አንጻር በ2015 ዓ.ም በተቋሙ ሊሰሩ የታቀዱ ዋና ዋና ስራዎች በዩኒቨርሲቲዉ የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ሰላም ተ/ሚካኤል ማብራርያ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ዳይሬክተሯ ለስራ ሂደቱ ከፍተኛ አመራሩ እያሳየ ያለዉን ድጋፍ በማመስገን ወደፊትም አመራሩ ድጋፍን እንዳያቋርጥ በማሳሰብ የእለቱ ፕሮግራም ተጠናቋል፡፡





## የስልጠናና ማማከር ዘርፍ በሴክተር-ተኮርና የብቃት-ተኮር

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የስልጠናና ማማከር ዘርፍ «በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሴክተር-ተኮርና የብቃት-ተኮር የስልጠናና የማማከር አገልግሎት አሰጣጥ፤ ፋይዳና የወደፊት አቅጣጫ» በሚል ርዕስ በቀን ታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ አውደ-ጥናት አካሄደ፡፡







ዶ/ር ዋቅጋሪ ነጋሪ የስ/ ማ ዘርፍ ም/ል ፕሬዚደንት

የአውደጥናቱ ዋነኛ ትኩረትም የመንግስት ሰራተኞችን አቅም በመገንባት ረገድ በተቋሙ እስከአሁን ምን ምን ተግባራት እንደተከናወኑ ግንዛቤን በመያዝ በቀጣይ ለሚከናወኑ ተግባራት ግልጽ የሆነ አቅጣጫ በማስቀመጥ ለመንቀሳቀስ ያለመ ሲሆን በአውደ ጥናቱ ላይም የተለያ የባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡ በአውደ ጥናቱ መክፈቻ ላይ የስልጠናና ማማከር ዘርፍ ም/ል ፕሬዚደንት ዶ/ር ዋቅጋሪ ነጋሪ የአውደ ጥናቱ ተሳተፊዎቸን በአውደ ጥናቱ ላይ በመገኘታቸው አመስግነው በጋራ በመመካከርና ለወደፊት ስራዎችን በጋራ አቅዶ ለማሳካት አውደ ጥናቱ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር ዋቅጋሪ አክለውም «ሴክተርና ብቃት ተኮር ስልጠናና ማማከር አገልግሎት መስጠትን ስናስብ ከተለመደው አስተሳሰብ በመውጣት አዲስና የአሰራር ስርዓትን የሚለውጥ አስተሳሰብ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡» ብለዋል፡፡

በመቀጠልም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሴክተር-ተኮርና የብቃት-ተኮር የስልጠናና የማማከር አገልግሎት አሰጣጥ፤ ፋይዳና የወደፊት አቅጣጫ ላይ ያተኮረ የውይይት መነሻ ጽሁፍ በወ/ሮ ሰብለ ሙሉጌታ የባለ ብዙ ዘርፍ ስልጠናና ማማከር ማዕከል ዳይሬክተር የቀረበ ሲሆን ዘርፍ በስሩ በሚገኙት አራት የስልጠናና ማማከር ማዕከላት

አማካይነት በርካታ ተግባራትን ማከናኑንና ያስመዘገበውን ውጤት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ እንዲሁም ወ/ሮ ኤደን ቡሽራ የስልጠና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በበኩላቸው ዘርፉ በስልጠናና የማማከር አገልግሎት



አሰጣጡ ላይ ከዚህ ቀደም ይከተለው የነበረውን አካሄድ በመገምገምና ክለሳ በማድርግ የብቃት ተኮር የስልጠና አሰጣጥ ሥነ-ዘዴን ለመተግበር መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻምበቀረበው መነሻ ጽሁፍ ላይ ከአውደ ጥናቱ ተሳታፎች የተለያዩ ሀሳቦችና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን በተነሱት ሀሳቦች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡





# ኢሲሰዩ የ2015 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ግምገማ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል የ2015 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ግምገማውን የዩኒቨርሲቲዉ የካዉንስል አባላት በተገኙበት ጥር 5 ቀን 2015 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ አካሄደ፡፡

በግምገማዉ መክፈቻ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ለካውስሉ አባላት ባደረጉት ንግግር በየሩብ ዓመቱ ጊዜውን ጠብቆ ሲካሄድ የነበረው የካውንስል ስብሰባ እና የዩኒቨርሲቲው የስራ ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በጥቅምት ወር በዩኒቨርሲቲው በተሰጠው የአስራ ሁለተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ምክንያት ባለመካሄዱ በዚህ ስብሰባ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የሥራ ክንውንን ጨምሮ አጠቃላይ የስድስት ወር የአፈጻጸም ሪፖረትት ቀርቦ ግምገማ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ ፕ/ር ፍቅሬ አክለውም ከታህሳስ 24 -27 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በዩኒቨርሲቲው የካውንስል አባላትና በአካዳሚክ ሠራተኞች “የምሁራን ሚና በሀገር ግናባታ” በሚል ርዕስ የምክክር መድረክ መካሄዱን አስታውሰው በተካሄደው የምክክር መድረክም ሁለት ዐበይት ጉዳዮች ላይ የበለጠ ጠንክሮ መስራት ተገቢ መሆኑ የተመላከተበት መድረክ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮችም በሀገሪቱ የሚገኙ የተቋማት ግንባታ እና አዲስ የፖለቲካ ባህል ማምጣት መሆኑን የጠቀሱት ፕ/ር ፍቅሬ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሌሎች ተቋማትን አቅም የሚገነባ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የራሱንም አቅም መገንባት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያለው የዩኒቨርሲቲ መዋቅርተከልሶ እና የተከለሰውም መዋቅር ጸድቆ ወደ ተግባር



ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት



የሚገባበት ደረጃ ላይ ይገኛል ብላዋል፡፡ በአዲሱ መዋቅር መሰረትም ዩኒቨርሲቲው በምርምር ዩኒቨርሲቲነት የተመደበ በመሆኑ በሶስት ዘርፎች ማለትም አስተዳደርና ልማት ዘርፍ፣ የአካዳሚክ ጉዳዮች ዘርፍ እና የምርምርና ትብብር ዘርፍ የተዋቀረ መሆኑን የገለጹት ፕ/ር ፍቅሬ ዩኒቨርስቲውን ወደ ላቀ ከፍታ ለማሸጋገርና የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት እንዲችል ከምንጊዜውም በበለጠ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጠንክሮ መስራት እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

በማስከተል የየዘርፉ ም/ፕሬዚደንቶች (የአካዳሚክ ፣የስልጠናና ማማከር፣የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና የአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ዘርፍ) እንዲሁም የፕሬዚደንት ጽ/ቤት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የስድስት ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖረታቸውን ለካውንስሉ አባላት በማቀረብ የካውንስሉ አባላት በቀረበው ሪፖረት ላይ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል፡፡

